# ለመሆኑ ሞት ምንድን ነው?

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

“እግዚአብሔር የመከራ ድሃ አይደለም!” አሉ የፍቅር እስከ መቃብሩ የበዛብህ አባት አቶ ቦጋለ መብራቱ ሚስታቸውን እመት ውድነሽ በጣሙን ሲመክሩ። [1] እናንተም “የባሰ እንዳይመጣ የበፊቱንም ሆነ የአሁኑን ሰቆቃ አታንሳብን” አትበሉኝ እንጅ በኔ እድሜ ያላችሁ ጦቢያውያን እንደምታውቁት ከልጅነታችን ጀምሮ የምናውቀው አንዱ በሌላው ሕይወት ላይ ወሳኝ ሆኖ አስሮ ሲያንገላታው፣ ንብረቱን ሲገፈው፣ እትብቱ ከተቀበረበት አገር አባሮ ሲያሰድደው፣ በኮረንቲ ሲጠብሰው፣ እንዲያም ሲል ሲገድለው ማየት ነው። “ለምሳ ሲያስቡን ለቁርስ አደረስናቸው” ይባል የነበረውን መግለጫ ብዙው ዜጋ የሚያስታውስ ይመስለኛል። ለነገሩ ምን የሚያስረሳ ነገር ተገኝቶ ይረሳል? እንዲያውም የዛሬውን ቁርስ ከትናንቱ የከፋ የሚያደርገው የቁርሱ መጥበሻ ምድጃ “ፍርድ ቤት” ተብሎ መጠራቱ ነው። በዚህ የምድር ሲኦል ምድጃ ውስጥ ስንቱ እንደ ድንች እየተጠበሰ፤ እንደ አሻሮ እየተቆላ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ህይወቱን እንዲያጣ ወይም እንዲሞት ተደርጓል፤ በመደረግ ላይም ይገኛል። ለመሆኑ ሞት ምንድን ነው?

አንድ ጎበዝ  “ሞት ምንድ ነው?” የሚለውን ጥያቄ ስጠይቀው በቂልነቴ በመገረም ከትከት ብሎ ስቆብኛል። ብዙውን ጊዜ ሞትን የምናያይዘው መቃብር ውስጥ ከመግባት ጋር ነው። አዎ ሞት ሲነሳ የሚታየን እንባ ማፍሰስ፣ ነጠላ መዘቅዘቅ፣ ደረት መድቃት፣ የሬሳ ሳጥን መሸከም፣ መቃብር መቆፈር፣ የሐዘን ንፍሮ መብላት፣ ፍታት፣ ተስካር፣ ሙት-አመት የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው። እርግጥ ነው በአብዛኛው ሞትን ቀደም ሲል በምድር ላይ የነበረ ሰው በምድር ውስጥ ከመግባት ጋር እናያይዘዋለን። ከዚህ ወጣ ስንልም ዛሬ ትርጉሙ “ከመንኩሰ ሞተ” ወደ መንኩሰ ጠበደለ እስከተለወጠበት ጊዜ ድረስ ምንኩስናም ስጋን ከአለማዊ ነገር ፍጹም አግልሎ መኖርን ስለሚጠይቅ እንደ ሞት ይቆጠር ነበር። በአደጉት አገሮች ሞት ህጋዊ ትርጓሜም(legal definition) አለው። እንደኔ እንደኔ የኔ ቢጤው ተራ ሰው በህይወቱ ሁለት አይነት ሞት ሊገጥመው ይችላል። አካላዊ(biological)ሞትና ስብእናዊ (humanstic) ሞት።

በሥነ-ህይወት ጥናት ወይም በህክምና ዓለም ሳይቀር የአካለዊ ሞት ትርጉም ብዙ ጊዜ አከራካሪ ነው። አንዳንዶች ሞትን ከልብ ምት ማቆም ጋር ሲያያይዙት ሌሎች ደግሞ ከአንጎል ስራ ማቆም ጋር ያስተሳስሩታል። ሌሎች እንደዚሁ ከእስተንፋስ ሰጥ ማለት ጋር ያቆራኙታል። [2,3] ለምሳሌ በአሜሪካን የሐኪሞች ማህበር የጸደቀው የአካላዊ ሞት ትርጉም እንደዚህ ይነበባል። “በዘመኑ ባለው የህክምና ቴክኖሎጅ ተጠቅመው የሰው የደም ዝውውርና እስተንፋስ ሊመለስ ባማይችል መልኩ ከቆመ ወይም ጠቅላላ አንጎሉ ማንኛውንም ስራ መስራት ከተወ አንድ ሰው ሞተ ይባላል።” (ትርጉም የራሴ) [4]  በዚህም ይሁን በዚያ አካላዊ ሞት በወቅቱ ባለው የቴክኖሎጅ ጥበብ ሊጠገን የማይችል የእስተንፋስ፣ የልብና የአንጎል አሰራር ማቆምን ያመለክታል። ዳሩ ግን ይህ አይነቱ ሞት በእኛ በሰው ልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን በጉንዳኑ፣ በዝንቡ፣ በአህያው፣ በበሬው፣ በአይጡ፣ በዝሆኑ፣ ወዘተ ላይ ሁሉ ይደርሳል።  ይህ የሚያመለክተው እንደዚህ አይነቱ ሞት እንዲያውም እንደ እንደ ፍጡርነታችን ከሌሎች እንስሳት ጋር የሚያመሳስለን ባህሪ መሆኑን ነው።

የስብእና ሞት ባንጻሩ በሰው ልጅ ላይ ብቻ የሚደርስ ሞት ነው። የስብእናን ሞት ለመሞት የሰው ልጅ መቃብር ውስጥ መግባት የለበትም። ሰው እንዲሁ ጮማና ብርንዶ እየበላ፣ በውስኪ እየተራጨ፣ መኪና እየነዳም ሆነ የግል አውሮፕላን እያበረረ፣ እልፍኝና አዳራሽ ወይም ቪላ ቤት ውስጥ እየኖረ ሁሉ የስብእናዊ ሞትን ሊሞት ይችላል። የድሃን ጉረሮ እየዘጋን፣ ለነፍሰ-ገዳዮችና ዘራፊዎች እንደ ቁና ሆነን እያገለገልንና እግር እየሳምን በዚህ መልክ የስብእናን ሞት እየሞትን የአካል ሞትን በመጠበቅ ላይ ያለን ስንቶቻችን እንደሆን አምላክና ራሳችን እናውቀዋለን።  ለእኔ የሰው ልጅ የስብእና ሞት የሚሞተው አንዱ አምላክም ሆነ አንዱ “ሐይል” ሲፈጥረው ይዞት የወጣው አካሉ በሌሎች ቁጥጥር ስር ሆኖ በፈለገው መንገድ ሊጠቀምበት ሳይችል ሲቀር ነው። አእምሮውን፣ ምላሱን፣ ጆሮውን፣ አይኑን፣ እጁን፣ አፍንጫውንና ሌሎቹንም የተፈጥሮ ስጦታዎች በሚፈልገው መንገድና ቦታ መጠቀም ካልቻለ ከሰውነት ባህሪ ወጥቶ ወደ እንሰሳነት ወይም እቃነት ተቀይሯል ማለት ነው። ችንክር በል ማንን ልትጎዳ አትበሉኝና በኔ ሞት “እንዳትተነፍስ! አለዚያም እኔ በምልህ መንገድ ብቻ ተናገር!” እየተባለ የሚኖር ግብር የሚገብር ዜጋ ጆርባውን እየገረፉ አውድማ ውስጥ ከሚያዞሩት አፋን በገመድ ከታፈነ በሬ በምን ይለያል? በእነእገሊት ላይ የእድሜ ይፍታህ እስራት በእነእንተና ላይ ደግሞ የሞት ፍርድ ፍረድ!” የሚል ቀጭን ትእዛዝ የሚቀበል ለስሙ ጥቁር የለበሰ “ዳኛ”  ምሳር ውስጥ ከሚገባ ጠማማ ዛቢያ ወይም አንስተው ወፈጥ ላይ ጣል ከሚያደርጉት የድንጋይ መፍለጫ መዶሻ በምን ይለያል?

እንደ ሙሴ፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ ወዘተ ያሉ ሐዋርያትን እንተውና በአለም ላይ ታላላቅ የሚባሉት ሰዎች ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት አካላዊ ሞትን ለመሸሽ ወይም ለማምለጥ ሳይሆን ሰብአዊ ሞትን ለማስወገድ ነበር። በእኔ እምነት “ቅዱስ” መባል ይገባዋል ብዬ የማምነው ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የርሱንም ሆነ የቤተሰቡን ህይወት መከራ

ውስጥ የጨመረው ከአካላዊ ሞት ለመዳን አልነበረም። ራሱንም ሆነ እንደ እርሱ በባርነት የሚማቅቁ ሰዎች እንደዚሁም እኔን ጨምሮ የዛሬም ሆነ የወደፊቱ የሰው ዘሮች ወደ እቃነት ከሚቀይር አሰቃቂ ስብእናዊ ሞት እንዲድኑ ነው። የህንዱ ኢንድራ ጋንዲ አካሉን በመከራ ሊጠበስ የኖረው አካላዊ ሞትን ለማስወገድ አይመስለኝም። እርሱም ሆነ የአገሩ ሕዝብ የሚበሉ የሚጠጡ እንስሶች ወይም በተፈለገው ቦታ እየተጎተቱ የሚያገለግሎ እቃዎች ሆነው እንዳይቀሩ እንጅ። ማንዴላ አካላዊ ሞትን ወደሚያፋጥነው እስር ቤት ገብቶ ሲማቅቅ የኖረው ስብእናዊ ሞትን ከርሱም ሆነ ከዘመዶቹ ጫንቃ ላይ ለማውረድ ሲል ነበር። አያት ቅድመ-አያቶቻችን መርዝ የሚረጭ ጠላትን የተጋፈጡት እነሱና እኛ እንደዚሁም የወደፊቱን ትውልድ ከስብእናዊ ሞት ለመከላከል ነበር። ራሳቸውን ከማይቀረው አካላዊ ሞት ለጊዜው ለማትረፍማ በዘመኑ እንደነበሩት ባንዶች አጎብድደው እየታዘዙና ወገኖቻቸውን እያስፈጁ ለአገልግሎታቸውም ፍርፋሪ እየተቀበሉ ቢቆዩ ይቀላቸው ነበር።

ዛሬም ፍትሐዊ ህግ በሌለባቸው እንደ አገራችን ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ሰዎች ንብረታቸውን የሚቀሙት፣ ከስራ የሚባረሩት፣ የሚሰደዱት፣ በእስር የሚንገላቱን፣ የሚገደሉት ስብእናዊ ሞትን ላለመሞት በሚያደርጉት ፍልሚያ ነው። አዎ ዛሬም በየጥሻው የሚንገላቱት ገበሬዎች፣ ለፍቶ አዳሪዎች፣ ተማሪዎች፣ ምሁራንና ሌሎችም ዜጎች በሰበብ አስባቡ "በቁርስ መጥበሻው ቦታ" የእድሜ ልክ እስራትና ሞት የሚበየንባቸው "ጭነት እንደሚጫን አጋሰስ ሰብአዊ መብታችንን ተገፈን ስንነዳ ከምንኖር የአካል ሞት ይሻለናል!" ብለው በወሰናቸው ይመስለኛል። እርግጥ ነው እንደነዚህ አይነት ሰዎች እንስሳ ወይም እቃ ከመሆን ራሳቸውን አውጥተው የማይቀረውን አካላዊ ሞት በመሞት ላይ ይገኛሉ። ቀሪዎቻችን ግን ስብእናዊ ሞትን ሞተን ወይም ወደ እንሰሳነትና እቃነት ተቀይረን የማይቀርልንን አካላዊ ሞት በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን። ጠለቅ ብለው ሲያስቡት ይገርማል! **በአንድ ሕይወት ሁለት ሞት!**

ከላይ እንደተገለጸው አካላዊ ሞት የፍጡራን(ህይወት ያላቸው ነገሮች) ሁሉ ባህሪ ነው። የወደፊቱን ባለውቅም እስካሁን ባለው የህክምና ጥበብ የሰው ልጅ አካላዊ ሞትን በትንሹ ማዘግየት ቢችልም ማስቀረት ግን ተስኖታል። ይህ ማለት ወደድንም ጠላም የሰው ልጅ ከመሞት አይድንም ማለት ነው። በሌላ በኩል ግን እንደ በሬ የሚያስጠምደንን ወይም ወደ አፍንጫ መጥረጊያ መሐረብነት የሚቀይረንን የስብእና ሞት መከላከልና ማስወገድ ይቻላል። ከግሪክ ጀምሮ በሌሎች የአውሮጳ አገሮች በትክክል ታይቷል። እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ከቁጥጥሩ ውጪ የሆነውንና ማንኛውም ፍጡራን የሚሞተውን አካላዊ ሞት በመሞቱ ተወቃሽነት አይኖርበትም። ስብእናዊ ሞትን ሞቶ እንደ እንሰሳ በመብላትና በመጠጣት ብቻ የኖረ፤ ወይም እንደ እቃ በሌሎች እጅ እየገባ ያገለገለ፤ አለዚያም በሌሎች ላይ አካላዊንም ሆነ ሰብአዊ ሞትን እንደ ዶፍ እያወረደ ከአውሬም የከፋ መልክ ይዞ የሚኖር ፍጡር ግን እስከ አለም ፍጻሜ ሲወቀስና ሲረገም ይኖራል። የሂትለርን፣ ኢዲ አሚንንና የአገልጋዮቻቸውን ታሪክ ለናሙና ያህል ያስታውሷል።

መቼም የሞት ጥሩ የለውምና ምናልባት ሁሉም የሞት አይነቶች ባይኖሩ መልካም ነበር። ዳሩ ግን እንደ አለመታደል ይሁን ወይም እንደ እርግማን አብዛኛው የአፍሪካ በተለይም የጦቢያ ሕዝብ ሁለቱንም የሞት አይነቶች እየተጎነጨ በመኖር ላይ ይገኛል። ጥቂት መንፈሰ-ብርቱዎች ብቻ ሰብአዊ ሞትን ድል ነስተዋል። አብዛኞቻችን ግን ማስወገድ ለምንችለው ለስብእናዊ ሞት ተንበርክከን የማናመልጠውን አካላዊ ሞት ትንሽ ለማዘግየት አንዴ የሚመገብ እንሰሳ ሌላ ጊዜ አገልጋይ እቃ እየሆን ጊዜ በመግፋት ላይ እንገኛለን። ስለዚህ ልቅሶና ሐዘን የሚያስፈልገው ለእኛ በከንቱ ሁለት ሞት ለምንሞተው እንጅ ጭራሽ የማይቀረውን አንድ አካላዊ ሞት እንዲሞቱ ለተፈረደባቸው፤ የክብር ቅኔና ዘፈን ለሚገባቸው፤ የስብእናን ሞት ድል ለነሱ፤ በስም፣ በግብርና በባህሪ ትክክለኛ ሰዎች ለሆኑ መንፈሰ-ጽኑ ዜጎች አይደለም። አመሰግናለሁ!

*ዋቢ*


1. *ፍቅር እስከ መቃብር መጀመሪያ እትም ገጽ 55*
2. *Sudden cardiac death* *http://dying.about.com/gi/dynamic/offsite.htm?zi=1/XJ&sdn=dying&zu=http%3A%2F%2Fwww.americanheart.org%2Fpresenter.jhtml%3Fidentifier%3D4741*
3. *Brain Death http://www.braindeath.org/clinical.htm*
4. *The definition of Death:* AMA. *1999;282:2367-2368.*


*ታህሳስ ሁለት ሺ ሁለት ዓ.ም.*